ኦክላንድ
ወረዳ ጤና ቦርድ

የሕዝብ ጤና

# መድሀኒተዎን ከመድሀኒት ቤት (ከፋርማሲ) ስለማግኘት

Amharic

# ሀኪሞዎን ሲጎበኙ፣ ሁሉንም መድሀኒቶቸዎን ይዘው በመሄድ ለሀኪሞዎ ያሳዩዋቸው።

## በሀኪም የታዘዘ መድሀኒት ከመድሀኒት ቤት እንዴት እንደሚገኝ

- ሀኪሞዎ ለአንዳንድ መዲሀኖቶች ማዘዣቅጽ (ፎርም) ይሰጠዎት ይሆናል - ይህም በሀኪም የታዘዘ መድሀኒት (ፕሪስክሪፕሽን) ይባላል።
- ከማንኛውም የመድሀኒት ቤት መሄድ ይችላሉ
- ሲሄዱም የሚከተሉትን ይያዙ፣
  1. የማዘዣውን ቅጽ (ፎርም)
  2. የማህበረሰባዊ አገልግሎት ካርድ ዎን (ኮሚዩኒቲ ሰርቪስስ ካርድ)
  3. የሚከፈል ገንዘብ
- የማዘዣ ቅጹን (ፎርሙን) በአስተናጋጆች ደስክ ላይ ላለው ሰው ይስጡ
- የማህበረሰባዊ አገልግሎት ካርደዎን ያሳዩ
- መድሃኒተዎ መቸ ዝግጁ እንደሚሆንለዎ ይጠይቁ

## መድሀኒተዎ ዝግጁ እንደሆነለዎ

- ወደአስተናጋጁ ደስክ ይመለሱ
- ስምዎን ይስጡ
- መድሀኒተዎን ይጠይቁ
- መድሀኒት ቀማሚው ሰው መድሀኒቶቹ መቸና እንዴት መወሰድ እንዳለባቸ ያብራራለዎታል
- ማንኛውንም ጥያቄ (ካለዎት) ይጠይቁ
- ለመድሀኒተዎ የሚጠየቁትን ክፍያ ይክፈሉ

## መድሀኒቶቹን ለመግዛት አቅመዎ የማይችል ከሆነ፣ ከአጠገበዎ ያለውንመድሀኒት ቀማሚ ወደሀኪመዎ ስልክ ደውሎ ሌላ የተሻለ ረከስ የሚልበት አማራጭ ካለ እንዲጠይቅለዎት ይጠይቁት

## በሀኪም ለሚታዘዙ መድሀኒቶች ክፍያዎች

- የማህበረሰባዊ አገልግሎት ካርድ ካለዎት በሀኪም ለሚታዘዙ አብዛሀኛዎቹ መድሀ ኒቶች የሚጠየቀው መደበኛ ዋጋ $3.00 ነው፣ ነገር ግን አንዳንዶቹ መድሀኒቶች ደግሞ ከዚህም በላይ ዋጋ ይጠይቃሉ።

- ከ6 ዓመት በታች ላሉ ሕጻናት አብዛሀኛዎቹ መድሀኒቶች በነጻ የሚሰጡ ና ችው።

- የማህበረሰባዊ አገልግሎት ካርድ ከሌለዎት፣ የእያንዳንዱ መድሀኒት ዋጋ $1 5.00 ይሆናል።

## የርዥም ጊዜ መድሀኒት (ህክምና)

- ለምሳሌ እንደ ስኳር በሽታ ላለ ህክምና ለረዥም ጊዜ የሚሆን የመድሀኒ ት ክትትል የሚያስፈልገዎት ከሆነ፣ ሀኪመዎ ለ3 ወራት የሚሆን አቅርቦትእ ንዲያገኙ በማዘዣው ቅጽ ያዝለዎታል።

- መድሀኒት ቀማሚውም የወሩን አቅርቦት ይሰጠዎታል።

- ይህን የመጀመሪያ ወር መድሀኒተዎን ከመጨረስዎ በፊት የምድሀኒቱን ብል ቃጥ ወይም ባኮውን ይዘው ወደ ቀማሚው ዘንድ በመውሰድ የሁለተኛ ውን ወር አቅርቦተዎን፣ ከዚያም በዚሁ መሰረት የሦሥተኛውን ወር አቅር ቦት ማግኘት ይችላሉ።

- በድጋሜ የሚወሰድ መድሀኒት ካለ፣ በባኮው ላይ "ድጋሜ" (ሪፒት) (Repeat) የሚል ቃል ይኖርበታል።

- በአጠቃላይ እርሰዎ መክፈል ያሚኖርበዎት የመጀመሪያውን ወር የመድሀኒት ዋጋ ብቻ ነው። የሁለተኛውና የሦሥተኛው ወራት መድሀኒቶችነጻ ናቸው።

# ባለክፍተኛ አገልግሎት የጤና ካርድ

- ከፍተኛ አገልግሎት (ጠቀሜታ) ያለው የጤና ካርድ አዘውትረው ወደሀኪም ለሚመላለሱ ሰዎች ለሀኪም ጉብኚታቸውና ለመዲሀኒት ግዢ የዋጋ ቅናሽ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

- ቀጣይነት ያለው የጤና ችግርን በተመለከተ የሀኪመዎን ምክር ለማግኘት ሲሉ በአመት ወ-ስጥ 12 ጊዚያት ወይም ከዚያም በላይ ወደሀኪመዎ የሚመላለሱ ከሆነ፣ ሀኪመዎ ይህን የባለክፍተኛ አገልግሎት የጤና ካርድ እንዲያገኙ ሊያመለክትለዎት ይችላል።

- ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘም፣ የባለከፍተኛ አገልግሎት የጤና ካርዱ ይላክለዎታል።

- ካርዶቹ በህጋዊነት አገልግሎት የሚሰጡት ለአንድ ዓመት ብቻ ስለሆነ ሀኪመዎ አዲሱን ካርደዎን እንዲያገኙ እንደገና ማመልከት ይኖርበታል።

AUCKLAND
DISTRICT HEALTH BOARD
Te Toka Tumai